ጋዜጣዊ መግለጫ
የአሜሪካ ኤምባሲ
አዲስ አበባ
2017/18

ለበለጠ መረጃ 011-130-7033
http://et.usembassy.gov

የአሜሪካ መንግሥት ለኢትዮጵያና ለኬንያ የ169 ሚሊዮን ዶላር ተጨማሪ የሰብዓዊ ዕርዳታ ይፋ አደረገ፡፡

ዋሽንግተን ዲ.ሲ ሐምሌ 27 ቀን 2009፡ የአሜሪካ መንግሥት በኢትዮጵያና በኬንያ በተከሰው የተራዘመና አስከፊ ድርቅ ተጠቂ ለሆኑ ዜጎች የሚውል ከ169 ሚሊዮን ዶላር በላይ ተጨማሪ የሰብዓዊ ዕርዳታ መለገሱን በዛሬው ዕለት ይፋ አደረገ፡፡ ይህ ለኢትዮጵያ የተደረገው 137 ሚሊዮን ዶላር እንዲሁም ለኬንያ 33 ሚሊዮን ዶላር የሚጠጋ ተጨማሪ ድጋፍ ጋር ተዳምሮ ፤ የአሜሪካ መንግሥት እ.አ.አ በ2017 ለኢትዮጵያና ለኬንያ የለገሰውን ድምር የሰብዓዊ ዕርዳታ መጠን 458 ሚሊዮን ዶላር ያደርሰዋል፡፡

ይህ ተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ የአሜሪካ መንግሥት የሚያደርገውን የአስቸኳይ የምግብ ዕርዳታ አቅርቦት ከማሳደጉም በላይ በምግብ ዕጥረት ለተጎዱ ሕጻናት የተመጣጠነ ምግብ በማቅረብ ክብካቤ ለማድረግ ያስችላል፡፡ በተጨማሪም ንጹሕ የመጠጥ ውኃና አስፈላጊ የጤና አገልግሎቶችን ለማቅረብ ይውላል፡፡ ይህ ዕርዳታ በኢትዮጵያ ለሚገኙና ወደ 3 ሚሊዮን ለሚጠጉ ሰዎች የሚደረገውን የ111,000 ሜትሪክ ቶን የምግብ እርዳታ ያካትታል፡፡ የአሜሪካ መንግሥት በድርቅ ከተጎዱ ኬንያውያን በተጨማሪ፤ በድርቅና በግጭት ምክንያት አገራቸውን ጥለው ወደ ኬንያ ለተሰደዱ ስደተኞችም ድጋፍ ያደርጋል፡፡

ይህ ተጨማሪ ዕርዳታ ወሳኝ በሆነ ወቅት የተደረገ ነው፡፡ በመላው ኢትዮጵያ ወደ 7.8 ሚሊዮን የሚጠጉ ሰዎች አስቸኳይ የሰብዓዊ ዕርዳታ ያስፈልጋቸዋል፡፡ በከፍተኛ ደረጃ በድርቅ በተጠቁ አካባቢዎች የሚገኙ አንዳንድ አባወራዎች፤ አስቸኳይና ቀጣይነት ያለው ድጋፍ ካልተደረገላቸው የምግብ እጥረቱ አስከፊ ደረጃ ሊደርስ እንደሚችል በአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት የሚደገፈው የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥርዓት መረብ ((FEWS NET) አስታውቋል፡፡ በድርቅ በተጠቁ አካባቢዎች ከአስከፊ ረሃብ በተጨማሪ ፤ የአጣዳፊ ተቅማጥና ትውከት በሽታ መስፋፋቱ፤ከረሃብ፣ ከምግብ እጥረትና ከተረጂዎች መፈናቀል ጋር ተዳምሮ አደገኛ ሥጋት ፈጥሯል፡፡ 2.6 ሚሊዮን ሕዝብ ከፍተኛ የምግብ ዋስትና አለመረጋገጥ ውስጥ በሚገኝበትና የምግብ እጥረት እያሻቀበ ባለበት ኬንያም ቢሆን የሰብዓዊ ዕርዳታ ፍላጎት እየጨመረ ነው፡፡

አሜሪካ ለኢትዮጵያና ኬንያ ከፍተኛ የሰብዓዊ ዕርዳታ ከሚለግሱ አገሮች **መካል አንዷ ስትሆን ፤ በዓለም ደረጃም** የሰብዓዊ ዕርዳታ በማቅረብ ቀዳሚውን ሥፍራ ይዛለች፡፡ በድርቁ የተጎዱ ሰዎችን ፍላጎት ለማማላት ፤ ኢትዮጵያ ፣ ኬንያና ሌሎች የሰብዓዊ ዕርዳታ ለጋሽ አገሮች ተጨማሪ ድጋፍ እንዲያደርጉ አሜሪካ ታበረታታለች፡፡

***

ስለ ዩ.ኤስ.ኤ.አይ.ዲና ስለፕሮግራሞቹ የበለጠ መረጃ ለማግኘት www.usaid.gov ይጎብኙ

የፕሬስ አድራሻ
ዩ.ኤስ.ኤ.አይ.ዲ *ፕሬስ ቢሮ*
ስልክ ቁ. +1.202.712.4320
ኢሜል፡ USAIDPressOfficers@usaid.gov

የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት (USAID) የአሜሪካ መንግሥት አስከፊ ድኅነትን ለማስወገድ እና ችግርን የመቋቋም ብቃት ያለውና ዴሞክራሲያዊ ሕብረተሰብ ለመገንባት የሚያደርገውን ጥረት በግንባር ቀደምትነት ይመራል፡፡